በአውቶቡስ ለመጓዝ

የ Metro ዌብ ሳይትን ይጠቀሙ፣ Metro Online በ www.kingcounty.gov/metro ላይ ወይም የሚጓዙበትን መስመር ለማግኘት፣ የአውቶብስዎን ማቆምያ ቦታ ለማወቅና ለጉዞዎ እቅድ ለማውጣት በ 206-553-3000 ይደውሉ።

በአውቶቡስ ማቆምያ ቦታው ላይ፣ የአውቶቡስ ማቆምያ በሚለው ምልክት ላይ የሚጓዙበትን የአውቶቡስ መስመር ይመልከቱ። አውቶቡሱ በሚመጣበት ወቅትም፣ ከአውቶቡሱ የፊት መስታወት በላይ የመስመርዎን ቁጥርና የመድረሻ ቦታዎን ስም ይመልከቱ። በአውቶቡሱ የፊት በር ገብተው መሣፈሪያዎን ይክፈሉ።

ፊት ለፊት ያሉት መቀመጫዎች ለአዛውንትና በአካል ለታጎሉ ሰዎች የተመደቡ ናቸው። ሰዎች ወደ መቀመጫቸው መሄድ እንዲችሉ፣ የአውቶቡሱን መተላለፍያ ነጻ ያድርጉ።

በ Metro አውቶቡሶች ላይ ለመጓዝ በጥሬ ገንዘብ፣ በ Metro ትራንስፈር፣ በ Metro ትኬት ወይም በ ORCA ካርድ መክፈል ይችላሉ። በአውቶቡሱ ውስጥ መሣፈሪያ መክፈያ ሳጥን ላይ የ ORCA ካርድዎን ማስነካት፣ ትክክለኛውን የገንዘብ መጠን ማስገባት፣ ወይም መሣፈሪያ ትኬት ለሾፌሩ ማሳየት ያስፈልግዎታል። ሾፌሮች ገንዘብ አይዙም።

አውቶቡሱ ወደ መድረሻዎ ቦታ ሲቃረብ፣ መውረድ እንደሚፈልጉ ለሾፌሩ ለማሳወቅ፣ ከመስተዋቱ በላይ ያለውን ገመድ ሳብ ያድርጉ።

መሣፈሪያ ዋጋዎች

Metro ሁለት "የዋጋ ዞኖች" አሉት። የ Seattle City የከተማ ክልልን አልፈው ከሄዱ፣ የሁለት-ዞን ዋጋ ይከፍላሉ። ሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች ላይ የትኬት ዋጋ ትንሽ ከፍ ይላል፣ ማለትም ከሰኞ - ዓርብ ጠዋት 6-9 a.m. እና ከሰዓት 3-6 p.m.

በ ORCA ካርድ መክፈል

ለመሣፈሪያ ትኬትዎ ለመክፈል የ ORCA የሚጠቀሙ ከሆነ፣ በአውቶቡሶችና በ Sound Transit ላይት ሬይል እና በባቡር ላይ መጓዝን በጣም ቀላል ያደርገዋል። የ ORCA ካርዱ፣ ለትኬትዎ መክፈያ የሚሆን ገንዘብ መሙላት የሚችሉበት "E-Purse" ("ሂሳብ ማጠራቀሚያ") በመሆን ሊያገለግል ይችላል። ወይም ደግሞ ወርሐዊ የአውቶቡስ መሳፈርያ ሊሞሉበትና ለአንድ ወር ያህል ላልተወሰነ ግዜ ሊጓዙበት ይችላሉ። የ ORCA ካርድ በ Metro የደምበኛ አገልግሎት ቢሮዎች፣ በላይት ሬይል ጣብያዎች ላይ ካሉ የትኬት መሸጫ ማሽኖች ላይ፣ በኢንተርኔት በ www.orcacard.com ላይ ወይም በስልክ ቁጥር 1-888-988-6722 ደውለው ሊገዙ ይችላሉ። የ ORCA ካርድ ገንዘብ ወይም ወርሐዊ መሣፈሪያ ሂሳብ ካልሞሉበት አያገለግልም።

ለአንድ አካባቢ የተፈቀደ ዝቅተኛ የትኬት ዋጋ (RRFP)

እድሜዎ 65 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ወይም በአካል የታጎሉ ከሆኑ፣ በዝቅተኛ የትኬት ዋጋ መጓዝ የሚያስችልዎትን የ RRFP ORCA ካርድን ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት Metro የደምበኛ አገልግሎትን ያነጋግሩ።

ሊፍት (አሳንሱር) ያላቸው አውቶቡሶች

ሁሉም የ Metro አውቶቡሶች፣ አዛውንትን፣ በአካል የታጎሉ ሰዎችንና የተሽከርካሪ ወንበር (ዊልቼር) የሚጠቀሙ ተጓዦችን ማስተናገድ የሚያስችሉ መጫኛ ወይም ሊፍት (አሳንሱር) አሏቸው።

የብስክሌት መጫኛ

ሁሉም የ Metro አውቶቡሶች እስከ ሶስት ብስክሌቶች መያዝ የሚችሉ የብስክሌት መጫኛ አላቸው። ብስክሌት ለመጫን ወይም ለማውረድ እቅድ ካለዎት ለሾፌሩ ያሳውቁ።

የግዜ ሰሌዳዎች

የአውቶቡስ የግዜ ሰሌዳዎች የጉዞ ግዜዎችን፣ መሣፈሪያ ዋጋዎችንና ካርታዎችን ያሳያሉ። በአውቶቡሱ ላይ፣ በቤተ መጻሕፍትና በገበያ አዳራሾች (ሞል)፣ እንዲሁም በ Metro የደምበኛ አገልግሎት ቢሮዎች ውስጥ ይገኛሉ።

በረዶማ የአየር ሁኔታ

በረዶ በሚኖርበት ወቅት፣ ወይም በድንገተኛ ሁኔታ ምክንያት የአውቶቡስ አገልግሎት ከተቋረጠ፣ በቋንቋዎ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት 206-553-3000 ይደውሉ።

Metro የደምበኛ አገልግሎት ቢሮዎች

King Street Center
201 S Jackson St, Seattle
ሰኞ – ዓርብ፣ 8 a.m. – 5 p.m.

ጠፍቶ የተገኘ
ሰኞ – ዓርብ፣ 9 a.m. – 1 p.m. እና 2 p.m. – 5 p.m.

Downtown Seattle Transit Tunnel
Westlake Station – 3rd Ave & Pine St

መረጃ
ስልክ.....206-553-3000 የመስማትና መናገር ችግር ላላቸው፣ 711 የማስተርጎም አገልግሎት አለ
Metro በኢንተርኔት....www.kingcounty.gov/metro